# የፖሊሲ አጭር መግለጫ ከ2007/2008 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ሥነ ሕዝብ እና የጤና ዳሰሳ ጥናት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ላይ በተገኙ ግኝቶች ላይ ተጨማሪ ትንተና

UNFPA

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Women, Children and Youth

UN WOMEN

# የፖሊሲ አጭር መግለጫ ከ2007/2008 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ሥነ ሕዝብ እና የጤና ዳሰሳ ጥናት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ላይ በተገኙ ግኝቶች ላይ ተጨማሪ ትንተና

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Women, Children and Youth

## መግቢያ

በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች (Violence against Women/ VAW) በቀጣይነት በሴቶች ላይ የሚፈጸም የሰብአዊ መብት ጥሰት ሲሆን በዓለም ደረጃም እንደ ወረርሺኝ በመስፋፋት ላይ ያለ የማኅበረሰብ ጤና ቁልፍ ችግር ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ3 ሴት መካከል 1ዷ (35%) ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ ሴቶች በቅርብ የትዳር ጓደኛቸው እና/ወይም የፍቅር ጓደኛቸው ባለሆነ ሰው በሕይወት ዘመናቸው አካላዊ ጥቃት እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል። ይበልጥ ዝርዝሩን ለማቅረብ ያክል፣ 30% በመቶ የሚሆኑ የትዳር ወይም የፍቅር ጓደኛ ያላቸው ሴቶች በሕይወት ዘመናቸው የቅርብ በሚሉት ይኸው የትዳር ወይም የፍቅር አጋራቸው አማካይነት አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሲሆን 7% የሚሆኑት ደግሞ በሕይወት ዘመናቸው የትዳር ወይም የፍቅር ጓደኛቸው ባልሆነ ሰው ወሲባዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል።[1] ከልጃገረዶች መካከል ከአምስቱ አንዷ በሕፃንነቷ ወሲባዊ ጥቃት የተፈጸመባት በመሆኑ ዕድሜያቸው 15 ዓመት ከመሆኑ በፊት ወሲባዊ ጥቃት የሚደርስባቸው ልጃገረዶችን ሁኔታ ሥር የሰደደ ችግር እንዲሆን አድርጎታል።[2]

እ.አ.አ በ2019፣ UNODC በሴቶች እና በልጃገረዶች ላይ የሚፈጸም የነፍስ ማጥፋት ወንጀል ከአጠቃላዩ በዓለም ዙሪያ ከሚፈጸም ግድያ 19% ብቻ የሚሸፍን ቢሆንም (ወንዶች ከአጠቃላዩ የጠፉ ነፍስ 81% ያክሉን ይይዛሉ) በቅርብ የትዳር አጋር/ጓደኛ/ቤተሰብ አባል ከሚፈጸም የነፍስ ማጥፋት ወንጀል በሴቶች እና በልጃገረዶች ላይ የሚፈጸመው 64% ሲደርስ በቅርብ የትዳር ጓደኛ/ፍቅረኛ የሚፈጸመው ግድያ መጠን 82% ይደርሳል (ወንዶች በቅርብ ወዳጃቸው/የትዳር አጋራቸው ወይም የቤተሰብ አባል የሚፈጸምባቸው ግድያ መጠን 36% ያክል ብቻ ሲሆን ከቅርብ የትዳር አጋር ወይም ፍቅረኛ የሚደርስባቸው የግድያ ጥቃት 18% ያክል ብቻ ነው)። እ.አ.አ በ2017 በአፍሪካ ውስጥ ከጠቅላላው ሟች ሴቶች መካከል በቅርብ ጓደኛቸው/ፍቅረኛቸው ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል ግድያ የተፈጸመባቸው መካከል ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት (69%) ሆን ተብሎ የተገደሉ ናቸው። ይህ ውሂብ ሴቶች እና ልጃገረዶች በቅርብ ትዳር ጓደኛ/ የቤተሰብ አባል የሚፈጸሙ ነፍስ ማጥፋት ወንጀሎች እና የቅርብ ትዳር አጋር ግድያዎች ትልቁን ቍጥር የሚይዙ ሰለባዎች እንደሆኑ ያሳያል።[3]

> **በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃት (Violence against Women/ VAW) እንደ "ማንኛውም ጾታን መሠረት ያደረገ በሴቶች ላይ አካላዊ፣ ወሲባዊ ወይም የሥነ-ልቦና ጥቃት ወይም ስቃይ የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል ድርጊት ሲሆን ሕዝብ በተሰበሰበባቸው ስፍራዎች ወይም በግል ሕይወት ውስጥ የሚከሰት ማንኛውም የማስፈራራት፣ የማስገደድ ወይም ማንኛውም መብትን የመከልከል ተግባር" እንደሆነ ተደርጎ ይተረጎማል።**
>
> **1993 Declaration on the Elimination of Violence Against Women (የ1993ቱ ዓለም አቀፍ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ማስወገድ ድንጋጌ)**

1 World Health Organization, London School of Hygiene and Tropical Medicine, and South African Medical Research Council (2013). Global and Regional Estimates of Violence Against Women: Prevalence and Health Effects of Intimate Partner Violence and Non-Partner Sexual Violence. World Health Organization: Geneva, Switzerland.

2 Haarr, R.N. (2081). ASEAN Regional Guidelines on Violence against Women and Girls Data Collection and Use. UN Women: Bangkok, Thailand.

3 *Global Study on Homicide: Gender-Related Killing of Women and Girls*, UNODC, 2019, p. 11.

በሴቶች ላይ ለሚደርሱ ጥቃቶች መንሥዔያቸውና የሚያስከትሉት ችግሮችም ሁሉ በቀጥታ ከሥርዓተ ጾታ እኩልነት አለመከበር ጋር የተገናኙ እንደሆነ የሚታመንበት ሲሆን ሴቶች እና ልጃገረዶች የሰብአዊ መብቶቻቸውን እንዳያስከብሩና በማኅበረሰቡና በኢኮኖሚው ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ዋንኛ እንቅፋት ነው። በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን የሚያስከትል አንድ የተለየ ብቸኛ ምክንያት የለም፤ ይልቁንስ ጥቃቶቹ የሚፈጸሙት በሴቶች እና በወንዶች መካከል በማኅበረሰቦች ውስጥ ባለ የሥልጣን ክፍፍል አለመመጣጠን እንዲሁም በዚህ የተነሣ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች እንዲፈጸሙ ምክንያት የሚሆኑና ጥቃቶቹን የሚያበረታቱ አድሎዋዊ እና የተዛቡ አመለካከቶች፣ ልማዶች እና ባህሎችን መከታ በማድረግ በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብ እና በተቋም ደረጃ የሚከናወኑ የተለያዩ ምክንያቶች ስብስብ ነው።

በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች በአደባባይ እና በድብቅ በሚፈጸሙ በአካላዊ፣ በወሲባዊ፣ ሥነ ልቦናዊ እና ኢኮኖሚያዊ የመብት ጥሰቶች የሚከፋፈሉ የተለያዩ ቅርጾችን ይዞ ይቀርባል። በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች የሴቶችን እና ልጃገረዶችን አእምሮ እና አካላዊ ጤና የሚጎዳ ከመሆኑ ባሻገር በደኅንነታቸው፣ መረጋጋት መቻላቸው እና በውስጣዊ ሰላማችወ ላይ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳርፍ ይችላል። በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ከዚህ በተጨማሪ ሴቶች በግላቸው እንዳይሻሻሉ እና በኢኮኖሚው ላይ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዳያደርጉ ሥር የሰደዱ ከባድ ችግሮችን ያስከትልባቸዋል።

በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች በኢትዮጵያ አዲስ የመጣ ክስተት አይደለም እንዲያውም በአባዊ ባህሎችና ልማዶች ውስጥ ለረዥም ጊዜ የቆየ ሥር የሰደደ ችግር ከመሆን አልፎ የተወሰኑ የሥርዓተ ጾታ ምንነቶችን እና ሚናዎችን፣ አባዊ የበላይነት፣ በቤተሰብ ውስጥ የሥልጣን ተዋረድ መዘርጋትን እና ከዘር ወደ ዘር የሚተላለፍ የበላይነትን ማስፈንን ጨምሮ በተለያየ መልኩ ይገለጻል። ጥራት ላለው የደኅንነት ጥበቃ፣ የጤና እንክብካቤ፣ የሥነ ልቦና እና ማኅበራዊ ድጋፍ፣ መጠለያ፣ የሕግ የምክር አገልግሎት መዳረሻ አለመኖር እና ፖሊስ እና የፍትሕ ሥርዓቱ የሚሰጧቸው ምላሾች አጥጋቢ አለመሆን ከዋንኛዎቹ እንቅፋቶችና በኢትዮጵያ ውስጥ የጾታ ጥቃት ሰለባ በሆኑ ሰዎች ዘንድ እንደ ምክንያት በዋንኛነት የሚጠቀሱ ናቸው።

የ2030ው ዘላቂነት ላለው ልማት አጀንዳ የሥርዓተ ጾታ እኩልነትን እና ዘላዊ ዕድገትን ለማረጋገጥ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ማስወገድ ዋንኛ ቅድሚያ ተሰጪ ነገር እንደሆነ አድርጎ ያስቀምጠዋል።[4] ከምንም በላይ ግን ዋናው ቁም ነገር፣ በሴቶች ላይ ለሚደርሱ ጥቃቶች መንሥዔያቸውና የሚያስከትሉት ችግሮችም ሁሉ በቀጥታ ከሥርዓተ ጾታ እኩልነት አለመከበር ጋር የተገናኙ እንደሆነ የሚታመንበት ሲሆን ሴቶች እና ልጃገረዶች የሰብአዊ መብቶቻቸውን እንዳያስከብሩና በማኅበረሰቡና በኢኮኖሚው ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ዋንኛ እንቅፋት ነው። በመሆኑም በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለማስቀረት መቻል የዘላቂ የልማት ግቦች (Sustainable Development Goals (SDGs)) ከምንም በላይ ቅድሚያ ተሰጪ ጉዳይ ሲሆን ምንም ድህነት የሌለበት፣ ጥሩ ጤና የሰፈነበት፣ ጥራት ያለው ትምህርት የሚሰጥበት እና ዘላቂ ልማት ያላቸው ከተሞችን እና ማኅበረሰቦችን እንዲሁም ሰላም፣ ፍትሕ እና ጠንካራ ተቋማትን ከማቋቋምና ከመገንባት አንጻር SDGዎች እንዲሳኩ ለማድረግ ቁልፍ ሚና ይጫወታል።[5] የ2030ው አጀንዳ አሁን ያሉ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን መፍትሔ ለመስጠት የተዘጋጁ ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፎች ላይ በመመርኮዝ የሚጎለብት ሲሆን በተለይ ደግሞ ከነዚህ የሕግ ማዕቀፎች Convention on the Elimination of all Forms of Discrimination against Women (በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ሁሉም

4 UN General Assembly (2016). Intensification of efforts to eliminate all forms of violence against women and girls. Seventy-first session, Item 27 of the provisional agenda, Advancement of Women.

5 UN General Assembly (2016). Intensification of efforts to eliminate all forms of violence against women and girls. Seventy-first session: Item 27 of the provisional agenda Advancement of Women; Gender Equality and the Sustainable Development Goals in Asia and the Pacific: Baseline and pathways for transformative change by 2030, Asian Development Bank and UN Women, 2018. Pp. 103-104.

ዓይነት መድልዎችን ማስቀሪያ ዓለም አቀፍ ስምምነት እና የሴቶች ጉዳይ ኮሚሽን በሃምሳ ሰባተኛው ስብሰባው ላይ የደረሰባቸው መደምደሚያዎችን እዚህ ላይ መጥቀስ ይቻላል።

## በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለማስቆም የተዘጋጁ ብሔራዊ ማዕቀፎች

ምንም እንኳ ኢትዮጵያ ለየት ያሉ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ወይም የቤት ውስጥ ጥቃትን ለመካከል የወጡ ሕጎች ባይኖራትም፣ አሁን በሥራ ላይ ያሉ ሕጎች እንደ መሸጋገሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ ተደርገው ዳግመኛ ተቀርጸዋል።[6] የ1992ቱ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ (Revised Family Code (RFC) እና በ1997 የተሻሻለው ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ (Revised Criminal Code (RCC) ) በቤተሰብ እና በትዳር ውስጥ ከVAWG ረገድ የሴቶችን መብቶች ለማስጠበቅ እና የቤት ውስጥ ጥቃትን እንደ ወንጀል ድርጊት እንዲቆጠር በማድረግ እንዲሻሻሉ ተደርገዋል።[7] ሁለቱም ሕጎች፣ ከሌሎች ሕጎች ጋር በመተባበር በኢትዮጵያ የነገረ አውድ አገባብ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ዋንኛ ምክንያቶችን ለይቶ በሴቶች ላይ በሚደርሱ ጥቃቶች ዙሪያ ያሉትን ዋንኛ ነጥቦች ይዳስሳል።

ምንም እንኳ ወሲባዊ ጥቃት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ወሲባዊ ትንኮሳ እና ጎጂ ልማዶች በሕግ እንደ ወንጀል የሚያስጠይቁ ሕገወጥ ተግባራት ተደርገው ቢቀመጡም፣ መንግሥት እንዲህ ያሉትን ሕጎች በማስከበር የሚወስዳቸው እርምጃዎች ወጥነት የሚጎድላቸው ናቸው። የቤት ውስጥ ጥቃት እና አስገድዶ መድፈር ብዙውን ጊዜ በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ዝቅተኛ ቅድሚያ ተሰጪነት ደረጃ ያላቸው በመሆናቸው እና በዚህም ምክንያት በተወሰነ መልኩ ቀላል የማይባል መጉላላት እና የፍትሕ መዘግየት ችግር ምክንያት ለአንዲት የበሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ሰለባ የሆነች ሴት የሚያጋጥማት ተግዳሮት ወደ ፍትሕ አስከባሪ አካላት መዳረሻ ማጣት ነው።[8]

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሴቶች እና ሕፃናት የዘርፍ ዕድገት ዕቅድ (2016-2020) እና ሁለተኛውን የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን (ጂቲፒ) 2015/16 - 2019/200 እንዲረቀቁ እና በሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች እንዲቆይሙ የሚያስፈልጉ ቅድሚያ ተሰጪ አስቻይ የመመሪያ የሕግ ማዕቀፍ እና በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃትን ለማስቀረት የሚያስችሉ በብዙ ዘርፎች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የትብብር ሥራዎች ስምምነቶችን ተከትሎ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ወደፊት ሊያራምዱት የሚችሉ እርምጃዎችን ወስዷል። የኢትዮጵያ መንግሥት በተጨማሪ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለማስቀረት አሁን ላይ በግምገማ ሂደት ላይ ያሉ ሁለት ስትራቴጂዎችን በማዘጋጀት ወደፊት የሚያራምዱትን እነዚህን እርምጃዎች ወስዷል፡-[9]

- ለተቀናጀ እና ብዝሀ ዘርፍ ምላሽ መስጫ ስትራቴጂክ ዕቅድ (Strategic Plan for an Integrated and Multi-Sectoral Response) በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች (VAW/C) እና በኢትዮጵያ ለሕፃናት ፍትሕ የሚሰጠው ምላሽ – በሴቶች/ሕፃናት የሚደርሱ ጥቃቶችን (VAW/C) በመከላከል፣ ጥበቃ በማድረግ እና ጥቃቶች ሲፈጸሙ ምላሽ መስጠት በሚያስችሉ ዘዴዎች ላይ ያተኩራል።

6 Programme Document, Preventing and Responding to VAWG in Ethiopia, UN Women, 2019; Economic Commission for Africa (ECA) (2009) African Women's Report 2009: Measuring Gender Inequality in Africa: Experiences and Lessons from the African Gender and Development Index, ECA: Addis Ababa, Ethiopia

7 Programme Document, Preventing and Responding to VAWG in Ethiopia, UN Women, 2019.; Preliminary Gender Profile of Ethiopia, 2014. European Union/UN Women: Addis Ababa, Ethiopia, p. 20.

8 Programme Document, Preventing and Responding to VAWG in Ethiopia, UN Women, 2019.

9 ዝኒ ከማሁ፤ ሁለቱም ስትራቴጂዎች የአፈጻጸም ክፍለ ጊዜያቸውን አጠናቀዋል። ለተቀናጀ እና ብዝሀ ዘርፍ ምላሽ መስጫ ስትራቴጂክ ዕቅድ (Strategic Plan for an Integrated and Multi-Sectoral Response) እስከ 2008-9 የሚቆይ የነበረ ሲሆን በHTPዎች ላይ የወጣው ብሔራዊ ስትራቴጂ እና ድርጊት ዕቅዱ እስከ 2009-10 የሚቆይ ነበር።

- በኢትዮጵያ ውስጥ በሴቶች እና በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መከላከያ ብሔራዊ ስትራቴጂ እና የድርጊት ዕቅድ (2007-8) በሴቶች፣ ሕፃናት እና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር (ሴሕወሚ/ MoWCYA) ይመራል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን እና ጎጂ ልማዶችን በማስቀረት ላይ የሚያተኩረውን የሴቶች ልማት እና ለውጥ ስትራቴጂን በተጨማሪ አዘጋጅቷል። በስትራቴጂው ፓኬጅ ተለይተው የታወቁ አራቱ አርምጃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦ ግንዛቤ ማሳደግ፤ በሴቶች ላይ ጥቃት ሲፈጸም ሕግ የማስከበር ምላሾችን ማጠናከር፤ ለሴቶች ጥቃት ተጠቂዎች የሕግ ድጋፍ ተገኝነትን መጨመር፤ ለሴቶች ጥቃት ሰለባዎች የሚሰጡ የጤና ክብካቤ አገልግሎቶችን ማሻሻል፤ ለሴቶች ጥቃት ሰለባዎች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ መጠለያዎችን እና ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ ጥላ ሥር የሚያቀርቡ ማዕከላትን ማቋቋም፤ እና ማስፈጸሚያ ዘዴዎችን ማስተባበሪያዎች ማቋቋም።[10]

እነዚህ የተለያዩ ስትራቴጂዎች የሴቶችን እና ሕፃናትን መብቶች ለመጠበቅ ደጋፊ በሆኑ መዋቅሮች እንዲጠናከሩ ተደርገዋል። ለምሳሌ፦ የሴቶች፣ ሕፃናት እና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎች በፌደራል እና ክልል ደረጃ በፍትሕ አስተዳደር የመንግሥት መሥሪያቤቶች ውስጥ እንዲቋቋሙ ተደርገዋል (ለምሳሌ፣ ፖሊስ፣ የዓቃቤ ሕግ ቢሮዎች፣ እና የዳኝነት ተቋማት)። በአንዳንድ ክልሎች ውስጥ፣ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን እና የሕፃናትን እና ሴቶችን መብቶች የሚመለከቱ ልዩ አሃዶች ተቋቁመዋል።

ይህም በተለያዩ የፖሊስ አሃዶች ውስጥ የሕፃን እና ሴቶች ጥበቃ አሃዶችን፣ በፌደራል ወንጀለኛ መቅጫ ፍርድ ቤት ውስጥ በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃትን ለመመልከት ብቻ የተለየ ልዩ ችሎትን፣ ለሕፃናት ተስማሚ የሆኑ ፍርድ ቤቶችን፣ እና በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት ውስጥ በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን የሚመረምሩ ልዩ የወንጀል ምርመራ አሃዶችን (FOAG) እና ክልላዊ የፍትሕ ቢሮዎችን (BoJ) ያካትታል።[11]

## በኢትዮጵያ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች

የ2008/2009 EDHS (የሥነ ሕዝብና ጤና ዳሰሳ ጥናት) በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃትን ያካተተ የመጀመሪያው በብሔራዊ ደረጃ የተደረገ ጥናት ነበር፤ ከዚህ በ2008/2009 ከተደረገው EDHS በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ሁሉን አቀፍ ጠቅለል ያለ መረጃ (ውሂብ) አይገኝም ነበር። የ2008/2009 EDHS በኢትዮጵያ መንግሥት በተለይም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጥያቄ አቅራቢነት የተከናወነ ሆኖ የዳሰሳ ጥናቱን ያከናወነው ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ነበር። በሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ጥያቄ አቅራቢነትም በ2008/2009 EDHS ላይ የቤት ውስጥ ጥቃት ሞጁል እንዲታከልበት ተደርጓል።

## የሴቶች ናሙና

በ2008/2009 የተደረገው EDHS የቤት ውስጥ ጥቃት ሞጁል በድምሩ 5,860 በሆኑ ዕድሜያቸው ከ15-49 በሚሆኑ ሴቶች ላይ የተደረገ ጥናት ሲሆን ጥናቱ ከመደረጉ በፊት በጭራሽ አግብተው በማያውቁ እና በወቅቱ አግብተው የነበሩ እና/ወይም አግብተው የሚያውቁ ሴቶች አጋጥሚቸው የሚያውቅ ጥቃትን ጨምሮ ሴቶች በአጠቃላይ የሚያጋጥማቸውን ጥቃት ለመለካት ተሞክሯል። ከነዚህ የዳሰሳ ጥናት የተደረገባቸው ሴቶች መካከል ሃያ አራት በመቶ የሚሆኑት በጭራሽ ከጥናቱ በፊት አግብተው የማያውቁ ሲሆኑ 76% የሚሆኑት ደግሞ ያገቡ ወይም አግብተው የሚያውቁ ነበሩ (አግብተው ከሚያውቁት ሴቶች መካከል 87% የሚሆኑት በወቅቱ በትዳር ላይ የነበሩ ሲሆኑ 13% የሚሆኑት ከጥናቱ በፊት አግብተው የሚያውቁ ናቸው ለአብነት የተፋቱ ወይም ባላቸው የሞተባቸው ናቸው)።

---

10 ዝኒ ከማሁ።

11 ዝኒ ከማሁ።

## የአካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃት የሴቶች ተሞክሮዎች

ዕድሜያቸው ከ14-59 ከሚሆኑ ሴቶች መካከል ከ4ቱ ከአንድ በላይ (26%) ዕድሜያቸው 15 ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል። ከዚህ ቁጥር ላይ እንደገና 23% የሚሆኑት ሴቶች ዕድሜያቸው 15 ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ አካላዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሲሆኑ 15% የሚሆኑት የዳሰሳ ጥናቱ ከመደረጉ ቀደም ብለው ባሉት 12 ወራት ውስጥ አካላዊ ጥቃትን አስተናግደዋል (ወቅታዊ)። ከሴቶቹ መካከል ዐሥር በመቶ የሚሆኑት ሴቶች በሕይወታቸው የሆነ ወቅት ላይ ወሲባዊ ጥቃት ደርሶባቸው የሚያውቁ ሲሆኑ ከሴቶቹ መካከል 7% የሚሆኑት ዳሰሳ ጥናቱ በተደረገበት ወቅትም ወሲባዊ ጥቃት እየደረሰባቸው የነበሩ መሆናቸውን ገልጸዋል። አራት በመቶ የሚሆኑት ሴቶች በእርግዝና ወቅት አካላዊ ጥቃት አጋጥሟቸዋል።

ከዳሰሳ ጥናቱ በፊት አግብተው ከማያውቁና አካላዊ ጥቃት ዕድሜያቸው 15 ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የደረሰባቸው ሴቶች መካከል ጥቃቱን ያደረሱባቸው ብዙውን ጊዜ እህቶች/ወንድሞች (27%)፣ ሌሎች ዘመድ አዝማድ (14%)፣ አባቶች/እንጀራ አባቶች (13%)፣ መምህራን (11%) እና የቀድሞ ወንድ ፍቅረኞች (8%) ናቸው። ሌሎች ጥቃት አድራሾች ሥራ አሠሪዎች/ በሥራ ቦታ ላይ ያለ ሰው፣ እናቶች/እንጀራ እናቶች እና ሴት ልጆች/ወንድ ልጆች የሚገኙባቸው ቢሆኑም ብዛታቸው ያን ያክል ጉልህ አይደለም።

አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት ከደረሰባቸው አግብተው ከሚያውቁት ሴቶች መካከል አብዛኛዎቹ ጥቃቱን ያደረሱባቸው ባሎቻቸው/የትዳር አጋሮቻቸው (68%) እና የቀድሞ ባሎች/የትዳር አጋሮች (25%) እንደሆኑ ገልጸዋል። በተመሳሳይ መልኩ፣ ወሲባዊ ጥቃት ደርሶብናል ያሉት ያገቡ ወይም አግብተው የሚያውቁ ሴቶች ብዙውን ጊዜ ጥቃቱን ያደረሱባቸው ባሎቻቸው/የትዳር አጋሮቻቸው (69%) እና የቀድሞ ባሎች/የትዳር አጋሮች (30%) እንደሆኑ አሳውቀዋል።

## በትዳር ጓደኛ የሚደርስ ጥቃት የሴቶች ተሞክሮዎች

ሠንጠረዥ 1 ካገቡ 3 ሴቶች መካከል አንዱ (34%) በስሜታዊ፣ አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት አማካይነት በትዳር አጋር የሚደርስ ጥቃት አሁን ባሉ/ወይም በቅርቡ አብረው ከነበሩዋቸው ባሎች/የትዳር አጋሮች አማካይነት እንደተፈጸመባቸው አረጋግጠዋል። ይህን ይበልጥ ለማብራራት፣ ስሜታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ያገቡ ሴቶች 24%፣ አካላዊ ጥቃት የደረሰባቸው 24%፣ እና ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው 10% ያክል ናቸው።

| ሠንጠረዥ 1፦ ዕድሜያቸው ከ15-49 ከሆነ ባገቡ ሴቶች ላይ በትዳር አጋር የሚፈጸሙ ጥቃቶች ዓይነቶች (N=4,469) | | |
|---|---|---|
| | በጭራሽ አጋጥሟቸው የማያውቅ | ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ያጋጠማቸው |
| አሁን ባለ ባል/የትዳር አጋር አማካይነት የተፈጸመ የትዳር አጋር ጥቃት[1] | | |
| አካላዊ ጥቃት | 24% | 17% |
| ወሲባዊ ጥቃት | 10% | 8% |
| ስሜታዊ ጥቃት | 24% | 20% |
| አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት | 26% | 20% |
| ስሜታዊ፣ አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት | 34% | 27% |
| በማናቸውም ባል/የትዳር ጓደኛ የተፈጸመ የትዳር ጓደኛ ጥቃት | | |
| አካላዊ ጥቃት | 25% | 17% |

| | | |
|---|---|---|
| **ወሲባዊ ጥቃት** | 11% | 8% |
| **አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት** | 28% | 20% |
| **በማናቸውም ባል/የትዳር ጓደኛ የትዳር ቁጥጥር (3 ወይም ከዚያ በላይ የተወሰኑ ባሕሪያት)** | | |
| **አፋኝ ባሕሪያት** | 16% | |

ምንጭ፦ 2016 Ethiopia Demographic and Health Survey, p. 305 ።

አሁን ያለን በትዳር አጋር አማካይነት የሚፈጸም ጥቃትን በተመለከተ፣ ዕድሚያቸው ከ15-49 ከሆኑ ያገቡ 4 ሴቶች መካከል አንዱ (27%) ከዳሰሳ ጥናቱ የተደረገበት ጊዜ ቀደም ብሎ ባሉት 12 ወራት ውስጥ አሁን ባለ/በቅርብ ጊዜ በነበረ ባል/የትዳር አጋር አማካይነት ስሜታዊ፣ አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት መልክ በትዳር አጋር የሚፈጸም ጥቃት አጋጥሚታል (20% ጥናቱ በተደረገበት ወቅትም አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት እየተፈጸመባቸው ነበሩ)። ይህን ይበልጥ ለማብራራት፣ ካገቡ ሴቶች መካከል 20% የሚሆኑት ስሜታዊ ጥቃት ሲደርስባቸው ፣ 17% የሚሆኑት ጥናቱ በተደረገበት ወቅት አካላዊ ጥቃት እየደረሰባቸው ያሉ ሆነው 8% በወቅቱ ወሲባዊ ጥቃት እየደረሰባቸው ያሉ ነበሩ።


ሠንጠረዥ 1 በተጨማሪ አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት ከደረሰባቸው ሴቶች መካከል ከ4ቱ አንዱ በባል/በትዳር አጋር አማካይነት ጥቃቱ የደረሰባት መሆኑን (25% የሚሆኑት አካላዊ ጥቃትን ሲያስተናግዱ 11% የሚሆኑት ደግሞ ወሲባዊ ጥቃትን አስተናግደዋል) እንዲሁም ባለፉት 12 ወራት 20% የሚሆኑት በባሎቻቸው አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት እንደደረሰባቸው ያሳያል። በተጨማሪ፣ ከሴቶቹ መካከል 16% የሚሆኑት በባሎቻቸው ሦስት ወይም ከዚያ በላይ አፋኝ ባሕሪያት አማካይነት የሚደርስ ጭቆና ደርሶባቸዋል። በጣም ከተለመዱት አፋኝ ባሕሪያት መካከል በጣም የተለመዱት ሴቷ ከሌላ ወንድ ጋር በመነጋገሯ (39%) ባልየው/የትዳር አጋሯ መቅናት ወይም መናደድ እንዲሁም የት እንዳለች ሁልጊዜ ለማወቅ አጥብቆ መጠየቅ (33%) ናቸው።

## በትዳር ጓደኛ የሚደርስ ጥቃት በመገኛ አካባቢ

መገኛ አካባቢ (ክልል እና ከተማ/ገጠር) በትዳር ጓደኛ የሚደርስ ጥቃት የሴቶች ተሞክሮዎች ዋንኛ መገመቻ መሣሪያ ነው። በትዳር አጋር የሚፈጸም ጥቃት (ስሜታዊ፣ አካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃት) ይበልጥ በኦሮሚያ (38%)፣ ሐረሪ (37%)፣ አማራ (35%) እና ጋምቤላ (34%) ሲሆኑ ድርጊቱ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ የሚታይበት ክልል ሶማሌ (9%) ነው። ተመሳሳይ ሁኔታ በአካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ በትዳር ጓደኛ የሚፈጸም ጥቃት አዝማሚያ ይታያል። ዕድሚያቸው ከ15-49 የሚሆኑ ያገቡ ሴቶች በኦሮሚያ (33%)፣ በሐረሪ (28%) እና በጋምቤላ (28%) አሁን ባሉ/ቀደም ሲል በነበሩ ባሎቻቸው/የትዳር ጓደኞቻቸው አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት ሊደርስባቸው የመቻል ዕድላቸው ከፍተኛ ነው።[12] በተጨማሪ በኦሮሚያ (22%)፣ በሐረሪ (19%) እና በጋምቤላ (18%) የሚሆኑ ሴቶች አሁን ባሉ/ቀደም ሲል በነበሩ ባሎቻቸው/የትዳር ጓደኞቻቸው እጅ ሦስት ወይም ከዚያ በላይ አፋኝ ባሕሪያት ሊያጋጥማቸው የመቻል ዕድሉ ከፍተኛ ነው።

12 በትዳር አጋር የሚደርሱ ጥቃቶች የመከሰት ዕድል በተመለከተ የሚታዩት ክልላዊ ልዩነቶች በተወሰደው የናሙና መጠን፣ እንደ በክልሉ ያለው የብሔር ብሔረሰብ መልክ በመሳሰሉ በክልሉ ባለው የባህል ተጽዕኖ አማካይነት ተጽዕኖ ሊያርፍበት ይችላል። የናሙና መጠኖች በሐረሪ (n=10)፣ ጋምቤላ (n=13)፣ ድሬ ዳዋ (n=23)፣ አፋር (n=43)፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ (n=44)፣ ሶማሌ (n=132)፣ አዲስ አበባ (n=146) እና ትግራይ (n=316) የተወሰዱት ናሙናዎች በኦሮሚያ (n=1,746)፣ አማራ (n=1,085) እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል (n=913) ከተወሰዱት ናሙናዎች አንጻር ሲታዩ አነስተኛ ናቸው።

ቻርት 1፡፡ በትዳር ጓደኛ የሚደርስ ጥቃት በክልል




ምንጭ፡- Ethiopia Demographic and Health Survey 2016, p. 304-306.


የ2008/2009 EDHS በተጨማሪ በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች (35%) የሚሆኑት በከተማ ከሚኖሩት ሴቶች (28%) አንጻር ሲታዩ ይበልጥ በትዳር ጓደኛ ለሚፈጸም ስሜታዊ፣ አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት ተጋላጭ እንደሆኑ ደርሶበታል፡፡ በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች (28%) የሚሆኑት በከተማ ከሚኖሩት ሴቶች (20%) አንጻር ሲታዩ ይበልጥ በትዳር ጓደኛ ለሚፈጸም አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት ተጋላጭ ናቸው፡፡

እንዲህ ያለው መረጃ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚዘጋጁ ሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን የተመለከቱ ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች መረጃ ለመስጠት እና አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ሃብቶችና ግብዓቶች በየትኛዎቹ ቦታዎች ላይ መቅረብ እና መሻሻል እንዳለባቸው በማስረጃ ላይ የተመረኮዘ ውሳኔ ለመወሰን ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

## በሕፃንነት የሚያጋጥም ለትዳር ጓደኛ ጥቃት መጋለጥ

በቤት ውስጥ የሚፈጸም ጥቃትን በተመለከተ በተለያዩ ባህሎች ላይ የተደረገ አሁን ያለ ጥናት እንደሚያሳየው በሕፃንነት ለቤት ውስጥ ጥቃት ተጋላጭ መሆን በዐዋቂነት ዘመንም የሚዘልቅ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ያረጋግጣል።[13] ለሴቶች በሕፃንነት ዕድሜ እና ይህን ተከትሎ የቅርብ ሰው በሚሉት የትዳር አጋር የሚፈጸምባቸው ጥቃት መካከል ጠንካራ ግንኙነት ያለ ሲሆን በወንዶች በኩል ደግሞ በሕፃንነት ዕድሜ እያሉ በሚያጋጥማቸው የቤት ውስጥ ጥቃት እና ራሳቸው በኋላ ላይ በዐዋቂነት ዘመን በትዳር አጋራቸው ላይ በሚፈጽሙት ጥቃት መካከል ጠንካራ የሆነ ግንኙነት አለ።[14] በመሆኑም የ2008/2009 EDHS ሴቶች በሕፃንነታቸው ለቤት ውስጥ ጥቃት ተጋላጭ በመሆናቸው (አባቶች እናቶቻቸውን ሲደበድቡ መመልከት) እና ዐዋቂ ከሆኑ በኋላ በትዳር አጋሮቻቸው በሚፈጸምባቸው ጥቃት መካከል ግንኙነት እንዳለ መጠቆሙ ያን ያክል የሚገርም አይደለም።

ቻርት 2። በሕፃንነት እና በዐዋቂነት የሚያጋጥም ለትዳር ጓደኛ ጥቃት መጋለጥ መካከል በሴቶች መካከል ያለ ዝምድና




13 Howell, K.H., S.E. Barnes, L.E. Miller & S.A. Graham-Bermann (2016). Development variations in the impact of intimate partner violence exposure during childhood. Journal of Injury & Violence Research, Vol 8, No. 1, pp. 43-57; Smith-Marek, E.N. et al. (2015). Effects of Childhood Experiences of Family Violence on Adults Partner Violence: A Meta-Analytic Review. Journal of Family & Theory Review, Vol. 7, No., 4, pp. 498-519.

14 Howell, K.H., S.E. Barnes, L.E. Miller & S.A. Graham-Bermann (2016). Development variations in the impact of intimate partner violence exposure during childhood. Journal of Injury & Violence Research, Vol 8, No. 1, pp. 43-57; Smith-Marek, E.N. et al. (2015). Effects of Childhood Experiences of Family Violence on Adults Partner Violence: A Meta-Analytic Review. Journal of Family & Theory Review, Vol. 7, No., 4, pp. 498-519.

ምንጭ:- Ethiopia Demographic and Health Survey 2016.

ሠንጠረዥ 2 አባቶቻቸው እናቶቻቸውን ይደበድቡ የነበሩ ሴቶች (49%) አባቶቻቸው እናቶቻቸውን ሲደበድቡ አላየንም ካሉ ሴቶች (28%) ይልቅ ሲታዩ ዐዋቂ ከሆኑ በኋላ በትዳር አጋሮቻቸው የስሜት፣ የአካል፣ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት ሊያጋጥማቸው የመቻሉ ዕድል በከፍተኛ ደረጃ የሚታይ መሆኑን ያሳያል። አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት በትዳር አጋር ለሚፈጸምባቸው ሴቶችም ተመሳሳይ አዝማሚያ ይታያል። አባቶቻቸው እናቶቻቸው ሲደበድቡ የተመለከቱ ሴቶች አባቶቻቸው እናቶቻቸውን ሲደበድቡ ካልተመለከቱ ሴቶች አንጻር ሲታዩ ስሜታዊ ጥቃት (35%) እና አካላዊ ጥቃት (36%) ሊደርስባቸው የመቻሉ ዕድል ሁለት እጥፍ የላቀ ሲሆን አባቶቻቸው እናቶቻቸውን ሲደበድቡ ያልተመለከቱ በትዳር አጋሮቻቸው ጥቃት የሚደርስባቸው ስሜታዊ ጥቃት 19% እና አካላዊ ጥቃት 18% ያክል ነው።

## ከጥቃት ጋር የተገናኙ የአካል ጉዳቶች

የተደበደቡ ሴቶች ብዙውን ጊዜ ከትዳር አጋር ጥቃት ጋር የተገናኙ የአካል ጉዳቶችን እና ከአንድ ዓይነት በላይ ከጥቃት ጋር የተገናኘ የአካል ጉዳት ያጋጥማቸዋል። ወሲባዊ ጥቃት ካጋጠማቸው 4 ሴቶች መካከል አንዷ (28%) እና በትዳር አጋር የሚደርስ አካላዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች መካከል 24% አንድ ወይም ከዚያ በላይ ከጥቃት ጋር የተገናኙ የአካል ጉዳቶችን ያስተናግዳሉ። የተደበደቡ ሴቶች መፈንከት፣ ሰምበር እና/ወይም የቁስል ሕመም (22% የወሲባዊ ጥቃት ሰለባዎች እና 20% አካላዊ ጥቃት ሰለባዎች) ይበልጥ ሊያጋጥማቸው የሚችል ሲሆን 13% ሴቶች የአጥንት ስብራት፣ የጥርስ መውለቅ እና/ወይም ሌላ ከባድ የአካል ጉዳት ሲያጋጥማችው 10% የዓይን ጉዳት፣ ወለምታ፣ ውልቃት እና/ወይም ቃጠሎ ያጋጥማቸዋል።

## የባል አልኮል መጠቀም/አላግባብ መጠቀም እና የትዳር ጓደኛ ጥቃት


የባል አልኮል መጠቀም/አላግባብ መጠቀም እና የትዳር ጓደኛ ጥቃት መካከል ያለው ዝምድና በጣም የተወሳሰበ ነው።[15] በቤት ውስጥ ለሚፈጸም ጥቃት እስካሁን በሰፊው የታወቀው የተሳሳተ አጉል እምነት ወይም የተሳሳተ ግንዛቤ የቤት ውስጥ ጥቃት መንሥኤ አልኮል መጠጥ መጠጣት ተደርጎ ቢወሰድም ምንም እንኳ በደል የሚያደርሱ ባሎች/የትዳር ጓደኞች ጥቃትን ለማድረስ የተገፋፉት አልኮል በመጠጣታቸው መሆኑን ቢገልጹም በእውነቱ ዓለም ላይ ግን አልኮል የቤት ውስጥ ጥቃትን አያስከትልም።[16] የአንድ በደል አድራሽ አልኮል አጠቃቀም/ ወይም ከልክ በላይ አልኮል መውሰድ በትዳር ጓደኛ ላይ በሚደርሰው ጥቃት ጉዳት መጠን ላይ አስተዋጽዖ ሊኖረው ቢችልም እና በዳይ ባሎች/ የትዳር ጓደኞች ድርጊታቸውን የፈጸሙት በአልኮል ላይ ሊያሳብቡ ቢችሉም በዳይ ባሎች/ የትዳር ጓደኞች አልኮል ስለጠጡ ብቻ ጥቃትን አይፈጽሙም። በሌላ አነጋገር፣ አልኮል መጠጣት ብቻውን ጥቃት የሚያደርስ ባልን/ትዳር አጋርን ስሜቱን መቆጣጠር እንዳይችል አያደርገውም፤ እንዲያውም የቤት ውስጥ ጥቃት ጥቅም ላይ የሚውለው አንዱ በሌላው ላይ ያለውን ሥልጣን እና የበላይነት ለማረጋገጥ ነው፤ በመሆኑም ከቁጥጥር ውጭ መሆንን አይወክልም።

የ2008/2009 EDHS ስሜታዊ፣ አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት በትዳር አጋር ከደረሰባቸው ሴቶች መካከል 80% የሚሆኑት ባሎቻቸው/ትዳር አጋሮቻቸው ሰክረው እንደነበሩ ሪፖርት ማድረጋቸውን ደርሶበታል። ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የተደበደቡ ሴቶችም በተጨማሪ ባሎቻቸው/የትዳር ጓደኞቻቸው አንዳንድ ጊዜ ሰክረው እንደነበሩ ሪፖርት አድርገዋል (45%)። ባሎቻቸው አልኮል እንደሚጠጡ ሆኖም ግን እንዳልሰከሩ (32%) ሪፖርት ያደረጉ ሴቶች እና አልኮል እንደማይጠጡ ሪፖርት ያደረጉ ሴቶች (28%) ሁለቱም ስሜታዊ፣ አካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት ያጋጠማቸው ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ወይም ብዙውን ጊዜ የሚሰክሩ ባሎች ካሉዋቸው ሴቶች ያነሰ ብዛትና ተደጋጋሚነት ያለው ነው።

15 Leonard, K. (2009). Domestic violence and alcohol: what is known and what do we need to know to encourage environmental interventions? Journal of Substance Use, 6(4): 235-247; Graham, K. & M. Livingston (2011). The Relationship between Alcohol and Violence – Population, Contextual and Individual Research Approaches. Drug and Alcohol Review, 30(5): 453-457.

16 Leonard, K. (2009). Domestic violence and alcohol: what is known and what do we need to know to encourage environmental interventions? Journal of Substance Use, 6(4): 235-247.

ቻርት 3። የባል አልኮል መጠቀም/አላግባብ መጠቀም እና የትዳር ጓደኛ ጥቃት




ምንጭ፡- Ethiopia Demographic and Health Survey 2016.

## ሴቶች ጥቃት ለሚያደርሱባቸው ባሎቻቸው ያላቸው ፍርሃት

አፋኝ ባሕሪያት በባሎቻቸው/በትዳር ጓደኞቻቸው የሚደርስባቸው ሴቶች ብዙውን ጊዜ ባሎቻቸውን/የትዳር ጓደኞቻቸውን እንደሚፈሩ፣ በተለይም አፋኝ ባሕሪው የሴቶችን በነጻ የመንቀሳቀስ መብት፣ ውሳኔ የመስጠት ችሎታን ሲያግድ እና በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፍ ሆኖ ሲገኝ ይበልጥ ፍራቻቸው ይጨምራል። ሴቶች ጥቃት ለሚያደርሱባቸው ባሎቻቸው/ትዳር ጓደኞቻቸው ያላቸው ፍርሃት በሕይወታቸው ለሚደርስባቸው ጥቃት ከሌሎች እርዳታና እገዛን እንዳይጠይቁ አቅም በተጨማሪ ያሳጣቸዋል።


የ2008/2009 EDHS በባሎቻቸው/በትዳር አጋሮቻቸው ሦስት ወይም ከዚያ በላይ አፋኝ ባሕሪዎች ከሚያጋጥማቸው ሴቶች መካከል 45% ያክሉ ባሎቻቸውን እንደሚፈሩ (27% ብዙውን ጊዜ ይፈራሉ እና 18% አንዳንድ ጊዜ ይፈራሉ)፤ ከተደበደቡ ሴቶች መካከል 18% ብቻ ባሎቻቸውን/ትዳር አጋሮቻቸውን በጭራሽ የማይፈሩ ሆነው አግኝቷቸዋል።

ሴቶቹ ብዙውን ጊዜ ከሌላ ወንድ ጋር ሲነጋገሩ (81%) ባሎቻቸው/የትዳር አጋሮቻቸው እንደሚቀኑ ወይም እንደሚነደዱ ይህም ሲሆን እንደሚያስፈራቸው እንዲሁም የት እንዳሉ ሁልጊዜ ለማወቅ አጥብቀው እንደሚጠይቁ (84%) ያክሉ ሪፖርት በብዛት አድርገዋል።

## በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ሰለባዎች እገዛ የመፈለግ ባሕሪ

ሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ሰለባዎች ጥቃቱ የደረሰባቸው በትዳር እና በቤተሰብ አውድ ውስጥ ሆነ በአደባባይ ቢሆንም እገዛን ለማግኘት ጥያቄ ለማቅረብ ብዙውን ጊዜ ዳተኛ ናቸው። ሠንጠረዥ 4 ከ5 ሴቶች አንዷ ወይም ከአካላዊ እና/ወይም ወሲባዊ ጥቃት ከደረሰባቸው ሴቶች መካከል 23% የሚሆኑት ለደረሰባቸው ጥቃት የድረሱልኝ ጥሪ አቅርበዋል። በተነጻጻሪነት፣ ከሴቶቹ መካከል 89% ያክሉ እገዛ በጭራሽ አልጠየቁም፣ ከነዚህ መካከልም 66% እገዛ በጭራሽ አልጠየቁም ብቻ ሳይሆን ስለጉዳዩ ለማንም አልተናገሩም እና 11% የሚሆኦት በጭራሽ እገዛ አልጠየቁም ሆኖም ግን ለሌላ ሰው ችግሩን ተናግረዋል። እነዚህ ግኝቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ሰለባዎች መካከል አብዛኛዎቹ በጸጥታ እንደሚሰቃዩ እና ምንም ዓይነት ጥበቃ እንደማይደረግላቸው፣ ሕጋዊ እና ሰብአዊ መብቶቻቸው ለሆኑት አገልግሎቶች ወይም ፍትሕ መዳረሻ ሆነ እገዛ እንደማያገኙ ያሳያሉ።

ቻርት 4። በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ሰለባዎች እገዛ የመፈለግ ባሕሪ




ምንጭ፦ Ethiopia Demographic and Health Survey 2016.

ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ከራሳችው ቤተሰብ (31%) እና ከባሎቻቸው/ከትዳር አጋሮቻቸው ቤተሰቦች (14%) ጨምሮ ከቤተሰብ እገዛ ለማግኘት ሞክረዋል። አንዳንድ ሴቶች ኢ-መደበኛ ከሆኑ አውታረ መረቦች በተለይ ከጎረቤቶች (34%) በተጨማሪ እገዛ ያገኙ ቢሆንም ይህ ብቻ ሳይሆን ከጓደኞች (10%) እና ከሃይማኖት መሪዎች (6%) እገዛ አግኝተዋል። ብዛታቸው በጣም አነስ ያሉ የሴቶች ጥቃት ሰለባዎች ከመደበኛ አውታረ መረቦች ማለትም እንደ ፖሊስ (8%)፣ ጠበቆች (3%)፣ ማኅበራዊ ሥራ ድርጅቶች (2%) ወይም የጤና ክብካቤ ሠራተኞች (2%) እገዛ ለማግኘት ሞክረዋል።

## ሚስትን መደብደብ በተመለከተ ያሉ አመለካከቶች

በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃትን ለማስቆም ዋንኛው እንቅፋት በኢትዮጵያውያን ወንዶች እና ሴቶች በሁለቱም ዘንድ ያለ በሚስት ላይ የሚደርስ በደልን የመደገፍ አመለካከት ነው። ዕድሜያቸው ከ15-49 ከሚሆኑት ከሴቶች መካከል 63% እና ከወንዶች መካከል 28% ያክሉ ከተጠቀሱት አምስት ሁኔታዎች ቢያንስ በአንዱ ባል ሚስቱን ቢመታ አግባብነት እንዳለው የሚስማማ እምነት እንዳላቸው አረጋግጠዋል (ለምሳሌ ሚስትየዋ ምግቡን ካሳረረችው፣ ሚስትየዋ ባሏ ጋር ከተጨቃጨቀች፣ ሚስትየዋ ለባሏ ስትናገር ወደ ውጭ ከሄደች፣ ሚስትየዋ ልጆቿን ችላ ካለች፣ እና/ወይም ሚስትየዋ ከባሏ ጋር ወሲብ ለመፈጸም አሻፈረኝ ካለች)። ከነዚህ ከተጠቀሱት አምስት ሁኔታዎች ቢያንስ በአንዱ ሚስትን መደብደብ አግባብነት አለው ብለው የሚያምኑት ወንዶች መቶኛ በ1992/1993 ከነበረው EDHS 76% በ2008/2009 ወደ 28% ቀንሷል። በተመሳሳይ መልኩ የሴቶቹ መቶኛ (ምንም እንኳ እንደ ወንዶቹ ከፍተኛ ለውጥ ያሳየ ባይሆንም) ከ1992/93ቱ EDHS 85% ወደ 63% በ2008/2009 EDHS ላይ ቀንሷል። አሁንም ድረስ፣ የሚስትን መደብደብ በመደገፍ ረገድ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች 'አሳማኝ በሆኑ ምክንያቶች' ሲሆን በከፍተኛ ደረጃ የመደገፍ አዝማሚያ ይታይባቸዋል።

## ለ2013/2014 EDHS ጠቃሚ ምክሮች

ከየ2008/2009 EDHS በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃትን በተመለከተ ከውሂብ አሰባሰብ እና ትንታኔ ረገድ የሚወሰዱ ትምህርቶች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት እና አጋሮቹ ለ2013/2014 EDHS ዕቅድ እያወጡ ያሉ እንደመሆናቸው ጠቃሚ ምክሮችን ሊሰጥም ይችላል። ከነዚህ ጠቃሚ ምክሮች መካከል አንዳንዶቹ በአዲስ አበባ ውስጥ በግንቦት ወር 2011 በተደረገው ዓውደ ጥናት ላይ ተለይተው ታውቀው እንደ ቅድሚያ ተሰጪነታቸው ተዘርዝረው የተረጋገጡ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በሪፖርት አጻጻፍ ሂደቱ ላይ ተለይተው ታውቀዋል። ለእያንዳንዱ ጠቃሚ ምክር በዝርዝር የቀረበ ማብራሪያን ለማግኘት፣ Further Analysis of Findings on Violence against Women from the 2016 Ethiopia Demographic and Health Survey (2019) የተባለውን ሰነድ ይመልከቱ።

## የአጠናን ዘዴ እና ናሙና አወሳሰድ

1. ለእያንዳንዱ ክልል፣ ናሙና መጠኖች በሴቶች ላይ ለሚደርስ ጥቃት ክሱትነት ደረጃን በበቂ ሁኔታ ለመገመት የሚያስችሉ መሆን አለባቸው። ናሙና መጠኖቹ አሳማኝ የሆነ የሴቶች ጥቃት ክሱትነትን ደረጃ በብሔራዊ እና ከብሔራዊ ባነሰ እንዲሁም በክልል ደረጃ ለማነጻጸር በሚበቃ መልኩ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ቀጣዩ EDHS ላይ በቂ ናሙና መጠኖች መሰላት እንዳለባቸው እና ለእያንዳንዱ ክልል በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ሞጁል ለማፍለቅ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ይመከራል።

2. የቃለ መጠይቅ አድራጊዎችን ምርጫ እና ሥልጠና ማሻሻል። ጥያቄዎቹ ስሜትን የሚነኩ እንደመሆናቸው መጠን ብቃት ያላቸው ቃለ መጠይቅ አድራጊዎች መመረጥ አለባቸው እንዲሁም ሁሉም ቃለ መጠይቅ አድራጊዎች በሚገባ መሠልጠን እና ቃለ መጠይቁን ለማድረግ እና የሴቶችን መጠይቅ በብቃትና በውጤታማነት ለማስኬድ የሚያስፈልገው ችሎታ እና በራስ መተማመን መንፈስ እንዳላቸው ለማረጋገጥ በሚገባ የሠለጠኑ መሆን እና የዳሰሳ ጥናቱ ጥያቄዎችን በተለይም ሴቶች ስለደረሰባቸው ጥቃት የተመለከቱ ጥያቄዎችን አስቸጋሪነትና ከባድነት የተረዱ መሆን አለባቸው። ከዚህ በተጨማሪ ቃለ መጠየቅ አድራጊዎች እንዴት ጥያቄዎችን መጠየቅ እንዳለባቸው እና ሥርዓተ ጾታን ከግምት ባስገባ መልኩ እንዴት ከምላሽ ሰጪዎች ጋር መግባባት እንደሚችሉ እንዲሁም በተመሳሳይ ጊዜ መረጃን (ውሂብን) እንዴት (ያለ ስሕተት) መመዝገብ እንደሚችሉ መሠልጠን ያስፈልጋቸዋል። በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃትን በሚመረምሩበት ጊዜ መጠበቅ ያለባቸውን የሥነ ምግባር መርሆዎች በዓለም የጤና ድርጅት እና በተባበሩት መንግሥታት በተቀመጡት ዓለም አቀፍ የሥነ ምግባር መመሪያዎች መሠረት ማከናወን እንዲችሉኡ ሙሉ በሙሉ በተጨማሪ መሠልጠን ይኖርባቸዋል።

3. ለ2008/2009 EDHS በቴክኒክ ቡድኑ ውስጥ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የትምህርት ተቋማት የተገኙ በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ልዩ ባለሙያዎችን እና ተመራማሪዎችን ማካተት። በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት እና ጎጂ ባህላዊ ልማዶችን ጨምሮ ክልላዊ እና የተለያዩ ጎሣዎችን ጨምሮ በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ላይ የተለየ ዕውቀት ያላቸውን ከፍተኛ ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች በቴክኒክ ቡድኑ ውስጥ እንዲሳተፉ መጋበዝ እና በማኅበራዊ ሳይንስ የምርምር አደራረግ ስልቶች እና የዳሰሳ ጥናት አደራረግ ዘዴዎች መጠቀም እጅግ አስፈላጊ ነው።

4. ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች ለሆኑ ልጃገረዶች እና ዕድሜያቸው ከ49 በላይ ለሆኑ ሴቶች ያለውን የመረጃ ክፍተት መፍትሔ መስጠት። አንዳንድ በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ስርጭትን ለማወቅ የተደረጉ ጥናቶች ዕድሜያቸው እስከ 69 ወይም 74 የሚአርሱ ሴቶችን አካተዋል ከነዚህም መካከል እ.አ.አ በ2014 የተደረገው የአውሮፓ ኅብረት (አኅ) ለመሠረታዊ መብቶች የአውሮፓ ኅብረት ኤጀንሲ አማካይነት በሰፊው የተከናወነ ዳሰሳ ጥናት (ከዚህ በመቀጠል የ2014ቱ FRA EU - በVAW ላይ የተደረገ ሰፊ ዳሰሳ ጥናት በመባል የተጠቀሰው) ይገኝበታል። በሴቶች ላይ ስለሚደርስ ጥቃት ዕድሜያቸው 50 እና ከዚያ በላይ ከሆኑ ሴቶች ብዙ ማወቅ የሚቻል ነገር አለ።

ከሴት ልጅ ግርዛት (FGM/C) ስርጭት ጋር ስለሚገናኝ፣ ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ልጃገረዶችን ማግለል የሴት ልጅን ግርዛት (FGM/C) ወቅታዊ ስርጭት ይዞታ ለመረዳት በሚያስፈልገው ዕውቀት ላይ ክፍተትን ይፈጥራል፤ ይህ የ2013/2014 EDHS ዕቅድን በማውጣት ሂደት ላይ ከግምት ሊገባ ይገባዋል። ምንም እንኳ አንዳንድ መረጃ ሴቶችን ሴት ልጆቻቸው መገረዝ አለመገረዛቸውን፣ የተገረዙበትን ዕድሜ፣ እንዲሁም የተገረዙበትን ጊዜ በመጠየቅ መረጃውን ማግኘት ቢቻልም ከሴት ልጅ ግርዛት ጋር ለተገናኙ ሌሎች መረጃዎች እናቶች ሴት ልጆቻቸው በትክክል ምን እንዳጋጠማቸው ልጆቻቸውን ወክለው እንዲናገሩ አይፈቀድላቸውም።

5. በጎሣ ግጭቶች ምክንያት በአገር ውስጥ ለመፈናቀል የተገደዱ ሴቶች በዳሰሳ ጥናቱ እንዲሳተፉ ባለመደረጉ ሊፈጠር የሚችለውን የመረጃ ክፍተት መፍትሔ መስጠት። የ2013/2014 EDHS የናሙና አመራረጥ ማዕቀፍ በተለይ በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በሚኖሩባቸው ክልሎች ውስጥ የሚገኙ የተገለሉ ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ማካተት ቢችል እጅግ ጠቃሚ ይሆናል።

## የVAW ልኬቶች

6. በጋብቻ ዓውድ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ኢኮኖሚያዊ ጥቃትን መለኪያዎች UN Guidelines for Producing Statistics on Violence against Women ኢኮኖሚያዊ ጥቃቶች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ይመክራል። የ2008/2009 EDHS በጋብቻ ዓውድ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ኢኮኖሚያ ጥቃትን ስርጭት ደረጃ አልለካም። ወደ ፋይናንስ ግብዓቶችና ሃብቶች፣ መሬት (ቤት) እና ቋሚ ንብረት፣ የሥራ ዕድል እና ትምህርት፣ ከኢኮኖሚያዊ ደረጃ ጋር በቀጥታ ዝምድና ባላቸው ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ ሴቶች ያላቸውን ተሳትፎ የማድረግ መብት መከልከልን የመሳሰሉ እና እንደ ድጎማ እና የገንዘብ እርዳታ የመሳሰሉ ኢኮኖሚያዊ ኃላፊነቶችን ሆን ተብሎ ሴትዋ እንዳትሳተፍ በማድረግ ወደ ድህነት እና ችግር ውስጥ እንድትጋለጥ ማድረግ የመሳሰሉ ኢኮኖሚያዊ ጥቃቶችን መለካት አስፈላጊ ነው።

7. በጉልበት፣ በማስፈራራት እና በመሞከር (ሆኖም ያልተሳካ) ወሲባዊ ጥቃት እና አስገድዶ መድፈር እንዲሁም ያልተፈለገ ንክኪን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት ወሲባዊ ጥቃቶችን መለካት። የ2008/2009 EDHS በወሲባዊ ድርጊት ላይ መሳተፍን የሚለኩ ሦስት ጥያቄዎችን አካቶ ነበር ሆኖም ግን የትዳር አጋር ባልሆኑ እና የቅርብ ወዳጆች አማካይነት በተለይም ክብረነክ ወሲባዊ ንክኪ፣ ያለ ሴቷ ፈቃድ የሚፈጸም ወይም የሚሞከር ወሲባዊ ድርጊት፣ ወሲባዊ ትንኮሳ እና ያልተፈለገ ንክኪ የመሳሰሉ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ እና ያልተፈለጉ ወሲባዊ ባሕሪያትን ደረጃ አልለካም።

8. ዕድሜያቸው 15 ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ወሲባዊ ትንኮሳ ለደረሰባቸው ሴቶች መፍትሔ ለመስጠት የሚወሰዱ እርምጃዎች። በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ስርጭት ጥናቶች ያልተፈለጉ እና ጸያፍ የሆኑ የወሲባዊ ትንኮሳ የተወሰኑ ድርጊቶችን ሊሸፍኑ ይችላሉ። እነዚህ በአራት ሰፋፊ ቡድኖች ሊቦደኑ ይችላሉ፦[17] አካላዊ ትንኮሳ (ያልተፈለገ ንክኪ፣ ማቀፍ ወይም መሳም)፤ በንግግር የሚደረግ ትንኮሳ (ወሲባዊ አንደምታ ያላቸው፣ ጸያፍ አስተያየቶች ወይም ቀልዶች፤ የአንድን ሴት የግል ሕይወት ጥሰው የሚቀርቡ ወይም አካላዊ ቁመናዋን የተመለከቱ ጣልቃ ገብና ጸያፍ ጥያቄዎች)፤ በንግግር የማይገለጽ ትንኮሳ (ተገቢነት የሌለው፣ በሚያስፈራ መልኩ አፍጥጦ ማየት ወይም ፈዞ ማየት፤ ጸያፍ የሆኑ ወሲባዊ ግልጽነት የሚንጸባረቅባቸውን ሥዕሎች፣ ፎቶዎች ወይም ስጦታ ዕቃዎችን መስጠት ወይም እንዲያዩ መደረግ፤ የሆነ ሰው ብልግና በተሞላ ሁኔታ ራሱን እርቃኑን ማሳየት፤ ያልፍላጎት ወሲብ ቀስቃሽ ይዘት ያላቸውን ቁሳቁሶች ወይም ነገሮች እንዲመለከቱ ወይም እንዲያዩ መገደድ)፤ እና ሳይበር ትንኮሳ (ያልተፈለገ፣ ጸያፍ፣ ወሲባዊ አንደምታ ያላቸው ኢሜይሎችን ወይም ኤስኤምኤስ መልእክቶችን መቀበል፣ በማኅበራዊ አውታረ መረብ የድርር ጣቢያ ወይም የበይነ መረብ (ኢንተርኔት) ውይይት ክፍሎች ውስጥ ጸያፍ ግብዣ)።የወሲብ ትንኮሳ እና ጥቃት ሴቶች የሚደርስባቸውን ቦታዎች የትኛዎቹ እንደሆኑ ለማወቅ መለካት። የዳሰሳ ጥናቶችን በማዘጋጀት ሂደት ወቅት ከተወሰኑ የወሲባዊ ትንኮሳ እና/ወይም ጥቃት ጋር የተገናኙ ገጠመኞች ጋር ግንኙነት ያላቸው ቦታዎችን እንዲሁም ከአገሪቱ ዓውድ ጋር እንዲናበቡ የተደረጉ ቦታዎችን የተመለከቱ ጥያቄዎችን መጠየቅ አስፈላጊ ነው።

9. ስሜታዊ ጥቃት ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች። ስሜታዊ ጥቃት ጋር የተገናኙ ጥያቄዎች ተጨማሪ የስሜት ጥቃት ዓይነቶችን ማካተት እንዲችሉ መስፋፋት ይችላሉ።

10. አፋኝ ባሕሪያት ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች። እንደ የእርስዎ ባል/የትዳር አጋር የእርስዎን እጅ ስልክ፣ ኢሜይል ወይም የማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን መለያዎችን የይለፍ ቃል እንዲሰጡዋቸው ያስገድዱዎታል ወይ የሚሉ መሰልጥ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አሁን ባለው ማኅበርሰብ ሴቶች እያጋጠማቸው ያሉትን አፋኝ ባሕሪያት እንዲገልጹ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን መጠየቅ ጠቃሚነት አለው። የእርስዎ ባል/የትዳር አጋር የጤና እንክብካቤ እንዳያገኙ የሚከላከል አፋኝ ባሕሪያት ያሳይዎታል ወይ የሚል ጥያቄ በመጠየቅ ጥቃት ነክ ጉዳት ሲደርስባቸው የጤና እንክብካቤ እንዳያገኙ ከማድረግ ጋር ሊገናኝ ስለሚችል እንዲህ መሰሉን ጥያቄ መጠየቅ በተጨማሪ አስፈላጊ ይሆናል።

11. በእርግዝና ጊዜ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን እና እንዲህ ያለውን ጥቃት ፈጻሚዎችን መለካት። እርገዘው የሚያውቁ ሴቶችን ስለጥቃት የተመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ አስፈላጊ ነው (ነፍሰጡር እያሉ ተመትተው፣ በጥፊ ተጨለው፣ በእግር ተጠልዘው ወይም የአካል ጉዳት ደርሶብዎት ያውቃል? ይህ የተፈጠረው በመጨረሻው እርግዝናቸው ላይ ነበር? እርስዎ ነፍሰጡር እያሉ ሆድዎት ላይ በቦክስ ወይም በእርግጫ ተመትተው ነበር? እርስዎ ነፍሰጡር እያሉ አካላዊ ጉዳት ሊያስከትሉብዎት የሚችሉትን እነዚህን ነገሮች በእርስዎ ላይ የፈጸመው ማን ነው?) በእርግዝና ወቅት ያጋጠሙትን አካላዊ ጥቃት ዓይነቶች መጠነ ስፋት እና ጥልቀት ግንዛቤ ለመጨመር እና የጥቃት ፈጻሚዎቹን ማንነት ይበልጥ ለመረዳት።

12. ማኅበራዊ ልማዶች በሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ በሚፈጸም ጥቃት ላይ ያሉ አመለካከቶች አንጻር ሲለኩ። የሴቶችን ጥቃት ሊደርስባቸው የሚችለውን ስጋት መጠን ለመረዳት በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት በማኅበረሰቡ ውስጥ (ማኅበራዊ ልማዶች) ምን ያክል በቸልታ እንደሚታለፍ መረዳትን ይጠይቃል። የዳሰሳ ጥናት ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ወቅት፣ በማኅበራዊ ልማዶች፣ የግል አመለካከት እና ባሕሪያት መካከል ያሉትን ልዩነቶች መረዳት መቻል አስፈላጊ ነው። ማኅበራዊ ልማዶች በአንድ በተመረጠ ቡድን ውስጥ ምን የተለመደ እና ተገቢነት እንዳለው የሚያሳዩ በሰፊው ተቀባይነት ያላቸው እምነቶች ናቸው፤ ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚታሰቡ እምነቶች። ማኅበራዊ ልማዶች ሌሎች ስላላቸው አመለካከቶች እና ባሕሪያት ላይ ሊመረኮዙ ወይም ላይመረኮዙ

17 Violence against Women (በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች)፦ An EU-wide survey, 2014, pp. 96-97.

ይችላሉ።”18 በንጽጽር፣ ባሕሪያት አንድ ሰው በግልጽ የሚያደርገው ነገር ነው። ምንም እንኳ እምነቶች እና ባሕሪያት እርስ በርስ ግንኙነት ያላቸው ቢሆኑም፣ ብዙውን ጊዜ ባሕሪ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፈው ማኅበራዊ ልማድ ነው፤ እንዲሁም ባሕሪ ማኅበራዊ ልማድ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፍ ይችላል።19 ማኅበራዊ ልማድ የተጋራ እምነት ሲሆን፣ የግል አመለካከት ስንል “የሆነ ነገርን (ሰውን፣ ምልክትን፣ እምነትን፣ እቃን) ከተወሰነ ደግ አመለካከት ወይም ጥላቻ ጋር የመለካት አዝማሚያ ነው።”20 ማኅበራዊ ልማዶች ከአመለካከቱ ጋር ሲጋጩ፣ የግል አመለካከቶች በአንድ ጥናት የሚደርግበት ቡድን ውስጥ ያሉትን አብዛኛዎቹን ሰዎች ባሕሪ በቀጥታ ሊመራ የመቻል ዕድሉ አምብዛም ነው።21 ማኅበራዊ ልማዶች፣ የግል አመለካከቶች እና ባሕሪያት ሁሉም በግራ ሌላውን የሚያገሉ አይደሉም ሆኖም ግን ብዙውን ጊዜ አንዳቸው ሌላኛቸውን ያጠናክራሉ። በጊዜ ሂደት፣ አንድ ግለሰብ በማኅበራዊ ልማዶች ምክንያት (ማኅበረሰቡ ከሚጠብቃቸው ነገሮች አንጻር) የሚያደርገው ነገር ሌሎች ምን እንደሚያስቡ ከግምት ሳይገባ በውስጣዊ ፍላጎቶች ምክንያት ውስጣዊ ሊሆን እና ሊከበር ይችላል።22 የ2008/2009 EDHS የግል አመለካከቶችን እና ባሕሪያትን ለክቷል፤ ሆኖም ግን ማኅበራዊ ልማዶችን አልለካም። ማላዊ በተመድ ሴቶች ማላዊ በመደገፍ በሴቶች እና ልጃገረዶች[23] ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች በተመለከተ ያሉ ማኅበራዊ ልማዶችን ለማወቅ የተደረገ ጥናትን (Perceptions Study on Social Norms on Violence Against Women and Girls) ካከናወኑ የአፍሪካ አገሮች አንዷ ናት። ከቴክኒክ ድጋፍ ጋር፣ የተመድ ሴቶች ማላዊ Social Norms, Attitudes and Behaviours Survey on VAWG[24] የተባለ በጥናት ላይ የተመረኮዘ የዳሰሳ ጥናትን አዘጋጅቷል።

13. ከጥቃት ጋር የተገናኙ ጉዳቶች፣ ለሕክምና እርዳታ ያለ መዳረሻ፣ እና በሥራ ላይ የሚያጋጥሙ ሁከቶች መለኪያዎች። የሚከተሉትን ጨምሮ በተጨማሪ አውራጃ (ዲስትሪክት) ምድቦች ተጨማሪ ከጥቃት ጋር የተገናኙ የአካል ጉዳቶች፡- ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ በቀላሉ መበሳጨት፣ የመገለል ስሜት እና/ወይም እንቅልፍ ማጣት፣ መፈንከት፣ መላላጥ፣ ሕመሞች፣ መቅላት ወይም ማበጥ እና/ወይም ሌላ ቀላል የጉዳት ምልክቶች፤ የዓይን ጉዳት፣ ውልቃት፣ ወለምታ እና/ወይም ከመቃጠል የተነሣ የሚፈጠር ቁስል፣ የጭንቅላት መፈንከት፣ የራስ ቅል ስብራት እና/ወይም መስማት አለመቻል፤ የሆድ ጉዳቶች፣ ጥልቅ ቁስሎች፣ የተሰበሩ አጥንቶች፣ የወለቀ ጥርስ፣ በቃጠሎ ወይም ሌላ ከባድ ጉዳት ምክንያት የሚደርስ ሰምበር ወይም የተበላሸ ቆዳ፣ ማስታወስ ችሎታን ማጣት፣ ውርጃ፣ እና ቋሚ ጉዳት ወይም መልክ መባለሸት

14. ከጥቃት ጋር የተገናኙ የአካል ጉዳቶች የሚያጋጥሟቸው ሴቶች የሕክምና እርዳታ አስፈልጓቸው እንደሆነ (የሕክምና እርዳታ እንዳገኙ ወይም እንዳላገኙ) እና ለጤና ባለሙያው ጉዳቶቹ እንዴት ሊከሰቱ እንደቻሉ

18 Alexander-Scott, M., E. Bell & J. Holden (2016). DFID Guidance Notes: Shifting Social Norms to Tackle Violence Against Women and Girls. London: VAW Helpdesk, p. 11.

19 Ibid, p. 8

20 Ibid, p. 11; Heise, L. & K. Manji (2015). Introduction to Social Norms. Briefing Note for DFID. DFID: London, UK..

21 Ibid p. 11.

22 Alexander-Scott, M., E. Bell & J. Holden (2016). DFID Guidance Notes: Shifting Social Norms to Tackle Violence Against Women and Girls. London: VAW Helpdesk, p. 12.

23 Haarr, R.N. (2018). Perceptions Study on Social Norms on Violence Against Women and Girls, UN Women Malawi.

24 ይህ Social Norms, Attitudes and Behaviours Survey on VAWG የተባለ የዳሰሳ ጥናት በአምስት አውራጃዎች (ዲስትሪክቶች) በ692 ከአጠቃላዩ ሕዝብ በተውጣጡ ዐዋቂ ሰዎች ላይ፣ ዕድሜያቸው ከ18-49 በሆኑ ወንዶችና ሴቶች፣ እና የአካባቢ አመለካከትን ሊቀርጹ የሚችሉ መሪዎች (ባህላዊ መሪዎች፣ አለቆች፣ የእምነት ተቋማት መሪዎች) የአውራጃ (ዲስትሪክት) እና ማኅበረሰብ ሹሞች (የማኅበራዊ ዋስትና ባለሥልጣኖች፣ የአውራጃ ዕቅድ አወጣጥ ኃላፊዎች፣ የኤክስቴንስን ሹሞች፣ ፖሊስ የጥቃት ሰለባ ድጋፍ ሰጪ ሹሞች፣ የማኅበረሰብ የጥቃት ሰለባ ድጋፍ ሰጪ አሃድ ሹሞች፣ የእናት ቡድን አባላት፣ የጤና ክትትልና ቁጥጥር ረዳቶች እና መምህራን)፣ እና እንዲሁም በማኅበረሰብ ላይ የተመረኮዙ ድርጅቶች (የአባት ቡድኖች)።

መናገር አለመናገራቸውን መጠየቅ አለባቸው። በሥራ ላይ የሚደርሱ ሁከቶች (የሚከፈልበት እና የማይከፈልበት ሥራ፣ የቤት ውስጥ ሥራ እና ከቤት ውጭ ያለ ሥራ) እና በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች በሴቶች እና በቤተሰቦች ላይ የሚያስከትሉትን ወጪ መለካት አስፈላጊ ነው።

15. እገዛ የመፈለግ አባዜ እና ሁልጊዜ እገዛ የመፈለግ አባዜን የሚያስከትሉ ምክንያቶችን መለካት። እገዛ የመፈለግ አባዜ ጋር የተገናኘ ጥያቄ፣ በተለይ ሴቶች ከማን እገዛ እንደሚፈልጉ የተመለከቱ ጥያቄዎች በዚያች አገር ያሉ መደበኛ ምንጮች/ባለሥልጣናትን ማከል ይኖርባቸዋል። ጥቃት ሲደርስባቸው እገዛን የሚፈልጉ ሴቶች በተጨማሪ ለምን እገዛ እንደፈለጉ እንዲገልጹ ሊጠየቁ ይገባል፤ የቤት ጥቃት ስለደረሰባቸው ቤታቸውን ጥለው ወጥተው የሚያውቁ ከሆነ፣ ከቃለ መጠይቁ በፊት ባሉት 12 ወራት ውስጥ ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ የቤት ጥቃት ስላጋጠማቸው ቤት ጥለው ከወጡ ለምን ያክል ቀን/ሌሊት እንደወጡ የጊዜውን ርዝመት፣ ለመጨረሻ ጊዜ ከቤት ሲወጡ ለምን እንደወጡ ምክንያቱን እንዲሰጡ ጥያቄ ሊቀርብላቸው ይገባል። እገዛ የጠየቁ በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ሰለባዎች ላጋጠማቸው ጥቃት ለምን እገዛ እንዳልጠየቁ እንዲገልጹ ሊጠየቁ ይገባል።

16. የቤት ውስጥ ጥቃት በሕፃናት ላይ የሚያሳርፈውን ተጽዕኖ መለካት። በትዳር አጋር የሚደርስ የቢአት ውስጥ ጥቃት እያጋጠማቸው ያሉ ሴቶችን የቤት ውስጥ ጥቃቱ በልጆቻቸው ላይ እያደረሰ ያለው ጫና ካለ ምን እንደሚመስል እንዲያግብራሩ ሊጠየቁ ይገባል።

## የውሂብ ትንታኔ እና ሪፖርት አደራረግ

የEDHS በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ውሂብ (መረጃ) ተጨማሪ ትንታኔ ማግኘት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ከትንታኔዎቹ መካከል አንዳንዶቹ በሚከተሉት ጠቃሚ ምክሮች መሠረት ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

17. በጥቃት ዓይነት በመለየት ሴቶች የሚያጋጥሙዋቸውን የተወሰኑ የጥቃት ዓይነቶችን ብዛት ማስላት። ሴቶች አንድ ዓይነት ብቻ ጥቃት እንደማያጋጥማቸው ሆኖም ግን በርካታ ጥቃት ዓይነቶችን በአንዴ እንደሚያስተናግዱ ለማስረገጥ ሴቶች የሚያጋጥማቸውን ስሜታዊ፣ አካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃት እንዲሁም አፋኝ ባሕሪያት በብዛት ለይቶ ማስቀመጥ።

18. በትዳር ጓደኛ የሚደርስ ጥቃት የተለያዩ ዓይነቶች መካከል ያለውን ግንኙነት መተንተን። አንባቢዎች በስሜታዊ፣ በአካላዊ እና በወሲባዊ ጥቃት እንዲሁም በአፋኝ ባሕሪያት መካከል በሴቶች ሕይወት ውስጥ ሕፃንነትን እና ዓዋቂነትን ጊዜ ጨምሮ እንዲሁም በእነርሱ ጋብቻ ሕይወት/የፍቅር ሕይወት ውስጥ ያላቸውን ዝምድና እንዲረዱ ለማገዝ።

19. በተደበደቡ ሴቶች ከጥቃት ጋር የተገናኙ የአካል ጉዳቶች ብዛት ድምርን ማስላት። የተደበደቡ ሴቶች ብዙውን ጊዜ ከአንድ በላይ ከጥቃት ጋር የተገናኙ የአካል ጉዳቶች ስለሚያጋጥማቸው ከቃለ መጠይቁ በፊት ባሉት 12 ወራት ውስጥ በተደበደቡ ሴቶች ላይ ያጋጠሙ ከጥቃት ጋር የተገናኙ የአካል ጉዳቶች አጠቃላይ ብዛትን ማስላት አስፈላጊ ነው።

20. በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ምክንያት የጠፋ ምርታማነትን እና ኢኮኖሚያዊ ኪሳራን መተንተን። በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ለሴቶች፣ ለቤተሰቦች፣ ለንግድ ድርጅቶች፣ ለኢኮኖሚው እና ለማኅበረሰቡ በአጠቃላይ ከፍተኛ ግምት ያለውን ኪሣራ የሚያስከትል የኢኮኖሚ ችግር ነው። በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት እገዛን ለማግኘት በሚያስፈልገው ወጪ እና የሚከፈልበት እና የማይከፈልበትን ሥራ ጨምሮ ከሥራ በመቅረት የሚደርስ ኪሣራ ምክንያት ጥቃት ያጋጠማቸው ሴቶች የገቢ ኪሣራ እና የግል ኪሣራዎችን ያስከትልባቸዋል።

21. በወሲባዊ ጥቃት፣ የወሊድ መከላከያ አጠቃቀም እና በግብረ ሥጋ አማካይነት የሚተላለፉ በሽታዎች (STIዎች) መካከል ያለውን ዝምድና መተንተን። በተለይ በባሎች/በትዳር አጋሮች የወሲብ ጥቃት የሚደርስባቸው ሴቶች፣ እና የወሊድ መከላከያ በሚጠቀሙ ሴቶች እና STIዎች የመያዝ ዕድላቸው መካከል ያለውን ዝምድና መተንተን አስፈላጊ ነው።

22. የአልኮል መጠቀም/አላግባብ መጠቀም እና የቤት ውስጥ ጥቃት መካከል ያለውን ዝምድና ትንታኔ ይስጡበት። ባሎች/የትዳር አጋሮች አልኮል አጠቃቀም/ አላግባብ መጥቀም፣ በተለይም ምን ያክል ጊዜ በተደጋጋሚ እንደሚሰክሩ፣ እና የቤት ውስጥ ጥቃት የሚደርስባቸው ሴቶች እና ከጥቃት ጋር የተገናኙ ጉዳቶች መካከል ያለውን ዝምድና መተንተን አስፈላጊ ነው።

23. የተለያየ ዓይነት ጥቃት ባጋጠማቸው ሴቶች መካከል ያለውን እገዛ የመጠየቅ አዝማሚያ እንዴት እንደሆነ መተንተን። ሴቶች የሚደርሳባቸው የጥቃት ዓይነቶች እንዴት እነርሱ እገዛ መጠየቅ መቻል አለመቻላቸው ላይ ተጽዕኖ እንደሚፈጥሩ መረዳት አስፈላጊ ነው፤ በመሆኑም የተለያየ ዓይነት ጥቃት የሚደርስባቸው ሴቶች ከማን እገዛን እንደሚጠይቁ ጨምሮ ምን ያክል እገዛ የመፈለግ አዝማሚያ እንደሚያሳዩ ለመረዳት ውሂቡ (መረጃው) መተንተን አለበት።

24. በ2008/2009 እና በ2013/2014 EDHS ጥናቶች የተገኙት ግኝቶች በሴቶች ላይ ከሚደርስ ጥቃት ጋር ባለው ግንኙነት ልክ ንጽጽሮችን በማድረግ አጭር የምርምር ውጤት ማጠቃለያን ማዘጋጀት። ለወደፊቱ፣ ፖሊሲ አውጪዎች በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት በአገሪቱ ውስጥ ምን ያክል እንደተስፋፋ እና የስርጭት መጠኑ ምን ያክል እንደጨመረ እና/ወይም እንደቀነሰ (በተለይ አሁን ባሉት በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት መጠን) በጊዜ ሂደት ከEVAW የሥራ ውጥኖች አንጻር በማገናኘት በ2008/2009 እና በ2013/2014 EDHS ጥናቶች የተገኙት ግኝቶች በሴቶች ላይ ከሚደርስ ጥቃት ጋር ባለው ግንኙነት ልክ ንጽጽሮችን በማድረግ አጭር የምርምር ውጤት ማጠቃለያን ማዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል።

25. በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ላይ ተጨማሪ ምርምር እና ጥናቶች ያስፈልጋሉ። በዚህ ምዕራፍ ላይ የተገለጹት አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች በ2013/2014 EDHS ላይ መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ላያገኙ ይችሉ ይሆናል። ለወደፊቱ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የተለያዩ አውዶች ውስጥ በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃትን በጥልቀት ለመገንዘብ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ላይ ተጨማሪ ምርምር እና ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል።

## በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ የሚፈጸም ጥቃትን ለማብቃት ጠቃሚ ምክሮች

ለ CEDAW አጠቃላይ ምክሮች 35 (2017) ምላሽ የሚሰጡ ምክሮች በአጠቃላይ ጠቃሚ ምክሮች ላይ የተመረኮዙ 19 (1992) ሲሆኑ ከዚህ በተጨማሪ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ማግለል እና መድልዎን ለማስቀረት የተቋቋመ ኮሚቴ በደረሰባቸው መደምደምያ ትዝብቶች (አርባ ዘጠነኛው ስብሰባ 11 — 29 ጁላይ 2011)፣ ከየተባባሩት መንግሥታት ልማት እርዳታ ማዕቀፍ ለኢትዮጵያ 2016-2020 እና SDG 5፣ እንዲሁም ስምንተኛው በ CEDAW ኮሚቴ በኢትዮጵያ ላይ የተሰጠ መደምደሚያ ትዝብቶች (2017) ላይ የተመረኮዙ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጠቃሚ ምክር በዝርዝር የቀረበ ማብራሪያን ለማግኘት፣ Further Analysis of Findings on Violence against Women from the 2016 Ethiopia Demographic and Health Survey (2019) የተባለውን ሰነድ ይመልከቱ።

26. የኢትዮጵያ መንግሥት አስቻይ የሆነ የሕግ ማዕቀፍን እና የፖሊሲ ድባብን በEVAW ዙሪያ ከዓለም አቀፍ የ EVAW ስምምነቶች እና ደረጃ መስፈርቶች አንጻር ለመፍጠር እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል።[25] በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን የተመለከቱትን ጨምሮ በኢትዮጵያ ውስት አሁንም ድረስ ባሉት ሕጋዊ እና መተዳደሪያ ማዕቀፎች ውስጥ ክፍተቶች አሉ። ፌደራል እና ክልላዊ EVAW ሕጎችን እና ፖሊሲዎችን ከዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግ ውሳኔ ሰጪዎችን እና ፖሊሲ አውጪዎችን ለማሳመን እና ከጥቃት ነጻ የሆነ ሕይወትን ለመኖር ያለ መብትን ጨምሮ የሴቶች መብቶችን የሚጥሱ ጥቃቶችን ለማስቆም አስተዋጽዖ ሊያደርግ የሚችል ፖለቲካዊ እና ሕጋዊ ድባብ ለመፍጠር ቁልፍ ሚና ይጫወታል።[26]

27. የ EVAW ፖሊሲን ወደ ተግባር ለመተርጎም ውጤታማ የሆኑ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው። የ EVAW ፖሊሲን በውጤታማ መንገድ ወደ ተግባር መተርጎም መቻል የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን ባለሥልጣኖች፣ የመንግሥት ባለሥልጣኖች እና ተቀዳሚ አገልግሎት ሰጪዎችን የEVAW ሕግን እና ፖሊሲዎችን፣ ለሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች የሰለባዎች በርካታ ዘርፍ ያላቸው አገልግሎቶችን ማቅረቢያ ስልቶችን ማስተባበር አስፈላጊነትን እንዲረዱ የአቅም ግንባታ ሥራን መሥራት ያስፈልጋል። ተቀዳሚ አገልግሎት ሰጪዎች በተጨማሪ በሴቶች ላይ ጥቃት ሲደርስ እና ለሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ሰለባዎች እና ሰለባዋን መውቀስን ለማስቀረት የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠትን በተጨማሪ ይጠይቃል።

ፖሊሲን ወደ ተግባር መተርጎም ለVAW አጠቃላይ ዕይታ እና የተቀናጀ በርካታ ዘርፎችን ያቀፈ አቀራረብ እንዲሁም VAWን ለመከላከል የተደረገ ግስጋሴ፣ ለVAW ሰለባዎች ጥበቃ ማድረግ፣ የVAW ጥቃት ፈጻሚዎችን በሕግ ተጠያቂ ማድረግን በተጨማሪ ይጠይቃል። አስፈላጊ አገልግሎትን ማቅረብ እና ወደ ፍትሕ ሥርዓት መድረስ ላይ ያሉ ማነቆዎችን እና ክፍተቶችን ለየቶ ማወቅ እና መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል።

28. ሁሉም የVAW ሰለባዎች ጥራት ላለው አስፈላጊ አገልግሎቶች መዳረሻ እንዳላቸው ማረጋገጥ። ጥራት ያላቸው አስፈላጊ አገልግሎቶች ለሁሉም የVAW ሰለባዎች መቅረብ አለባቸው። ሥርዓተ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ላጋጠማቸው ለሁሉም ሴቶች እና ልጃገረዶች ጥራት ያለው በርካታ ዘርፎችን ያማከሉ አስፈላጊ አገልግሎቶችን በቅንጅት በታላቅ ስፋት ለማቅረብ እንዲቻል ከUnited Nations Joint Global Programme on Essential Services for Women and Girls Subject to Violence፣ ጋር በተጣጣመ መልኩ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ለVAW ሰለባዎች ጥራት ያላቸውን በርካታ ዘርፎችን ያማከሉ አስፈላጊ አገልግሎቶችን በተቀናጀ መልኩ በአንድ ላይ ማቅረብ እንዲችል ለብሔራዊው አስተባባሪ አካል ያለውን አቅሞች ማጠናከር።[27] በፌደራል ደረጃ የብሔራዊውን አስተባባሪ አካል ሥራ አፈጻጸም እና ችሎታዎች እንዲሁም በክልል ደረጃ የተልዕኮ ሥራ ማስፈጸሚያ ዘዲዎቹን እንዲሁ በንዑስ ክልላዊ ደረጃዎች ላይ ለVAW ሰለባዎች ጥራት ያላቸውን በርካታ ዘርፎችን ያማከሉ አስፈላጊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ እንዲቻል አቅማቸውን ማጠናከር አስፈላጊ ነው። ይህ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች እና ልጃገረዶች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎ

29. ቶች ፓኬጅ - ዋንኛ አባል ነገሮች እና የጥራት መመሪያዎች ላይ ለእነዚህ አካላት ሥልጠናዎችን ማቅረብን ያካትታል እንዲሁም በአስፈላጊ አገልግሎቶች ላይ ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን እና መመሪያዎችን ለማሟላት እና ለማካተት ቴክኒካዊ መመሪያ እና ድጋፍ ሊቀርብላቸው ይገባል።[28]

30. የኢትዮጵያ ሴቶች መጠለያዎች አውታረ መረብን (Ethiopia Network of Women's Shelters (ENWS) ለመደገፍ የማኅበረሰብ ልማዶችን (Community of Practice (CoP)) መደገፍ። የENWSA CoP ያጋጠሙ ተግዳሮቶች፣ ችግር መፍቻ መፍትሔዎች፣ እና የተገኙ ትምህርቶችን

25 Programme Document, Preventing and Responding to VAWG in Ethiopia, UN Women, 2019.

26 CEDAW general recommendation 28.

27 Programme Document, Preventing and Responding to VAWG in Ethiopia, UN Women, 2019.

28 ዝኒ ከማሁ።

በሴቶች መጠለያዎች መካከል ያሉትን መለኪያዎች እና ሌሎች የሰለባ ድጋፍ አገልግሎት አቅራቢዎች መካከል ያለ መላላክን ለማጠናከር ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። CoP ለVAW ሰለባዎች ጥራት ያለው አገልግሎትን ለማቅረብ የሚቻልበትን መንገድ ለማጠናከር በአጋርነት መሥራትን ሊያጠናክር ይችላል።

31. ሥርዓተ ጾታን ያማከለ ምላሽ ለመስጠት እና በሰለባ ላይ ያማከለ ምላሾችን ለመስጠት እንዲሁም ለVAW ሰለባዎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያስችል ዕውቀት፣ አመለካከት እና ክኅሎትን በተቀዳሚ አገልግሎት ሰጪዎች ዘንድ ለማሻሻል ሥልጠና መስጠት። ሥርዓተ ጾታን ያማከለ ምላሽ ለመስጠት እና በሰለባ ላይ ያማከለ ምላሾችን ለመስጠት እንዲሁም ለVAW ሰለባዎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያስችል ዕውቀት፣ አመለካከት እና ክኅሎትን በተቀዳሚ አገልግሎት ሰጪዎች ዘንድ ለማሻሻል ሥልጠናዎች መስጠት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

32. ማኅበራዊ ልማዶችን፣ አመለካከቶችን እና ባሕሪያትን ለመለወጥ ስለሁሉም ዓይነት VAW የባሕሪ ለውጥን ማሳደግ እና ግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን ማከናወን። ሁሉንም ዓይነት VAW ለማብቃት የሚያስችሉ ማኅብራዊ ልማዶችን ለማቋቋም የሚያስችሉ የልማት ስትራቴጂዎችን ማስረጃ ላይ በተመረኮዘ ተግባብቶት ማሳደግ። ይህ የተሳሳተ መረጃን እና በቅርብ ፍቅረኛ የሚደርስ ጥቃት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ አስገድዶ መድፈር/ወሲባዊ ጥቃት እና ወሲባዊ ጥቃት በአደባባይ እና በግል ሕይወት ከተገናኙ የተለመዱ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የሚያርቅ እና የባሕሪ ለውጥ ዘመቻዎች እና ስትራቴጂዎችን ያካትታል። እንዲህ ያሉ ዘመቻዎች VAW ሰለባዎች መብታቸውን እንዲያውቁ እንዲሁም ለVAW እገዛ እንዲሰጣቸው ጥያቄ እንዲያቀርቡ እንዲሁም የVAW ሰለባዎች ካገኙት እገዛ ስላገኙት ጥቅም እውነተኛ ታሪካቸውን እንዲያጋሩ ማበረታታት አለባቸው።

33. በVAW ላይ በሚኒስቴር እና በዘርፍ መሥሪያ ቤቶች ላይ ጥራት ያለው አስተዳደራዊ መረጃን መሰብሰብ። በVAW ላይ አስተዳደራዊ መረጃን አሰባሰብ ማጠናከር አስፈላጊ እና ጠቀሜታ ያለው ኢንቬስትመንት ነው።[29] አስተዳደራዊ ውሂብ (መረጃ) ታሪካዊ ሥርዓተ ጥለቶችን እና አዝማሚያዎችን ለይቶ በማወቅ፣ ሪፖርት በማድረግ እና ምላሽ በመስጠት ረገድ ለማሰስ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። በተግባር ደረጃ፣ ማኅበራዊ ዋስትናን፣ የጤና ክብካቤን፣ ፖሊስ እና የፍትሕ አገልግሎትን ጨምሮ ከማኅበረሰብ ላይ የተመረኮዙ አገልግሎቶችን አጠቃቀም ጋር መረጃው የአገልግሎቶችን አጠቃቀም በተግባር ለማሳየት አስተዳደራዊ ውሂብ አጠቃላይ የፕሮግራም ዕቅድ አወጣጥ እና የግብዓት ምደባን መረጃ ለመስጠት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።[30]

34. አጋርነትን እና ትብብር ሥራን ማጠናከር VAWን ለማስቆም ምርምር እና ፕሮግራም እንዲሁም ፖሊሲ ዝግጅትን ለማሻሻል ዓላማ የመንግሥት እና ሲቪክ ማኅበራት ተወካዮችን ጨምሮ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን፣ ዩኒቨርስቲዎችን፣ የምርምር ተቋማትን እና የግሉን ዘርፍ ጨምሮ በተለያዩ ተዛማጅነት ባላቸው ተቋማት፣ ድርጅቶች እና ኤጀንሲዎች መካከል ያለውን አጋርነት እና በቅንጅት መሥራት መቻል ሁኔታን ማጠናከር አስፈላጊ ነው።

29 ASEAN Regional Guidelines on Violence against Women and Girls – Data Collection and Use, UN Women, 2018.

30 ዝኒ ከማሁ።

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Women,
Children and Youth